# ዝምታው ይቁም

## ስያሚያችን ኢወክንድ

## ልሳናችን ነቅንቅ

የዓለም ወጣቶችን እንቅስቃሴ ገድል ስንፈትሽ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል ታሪክ ደኅስ ያለውን አኩሪ ምዕራፍ ይይዛል ፡፡ እነሆ የፊታችን ሳምንት አስገምጋሚው የየካቲት ስልሳ ስድሰት ዝክረ ትግል ይጠብቀናል ፡፡ የካቲት ስልሳ ስድስት ይደገም የሚል መግለጫ ባለፈው አወጥተን ነበር ዛሬ ደግሞ በቁርጠኝነት ይደገማል የሚለውን መፈክር ስናስተጋባ ከኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ አብራክ ተወልደን በአይገበሬው ኢሕአፓ ተኮትክተን ለዚህ የበቃን የኢትዮጵያ ወጣት ደጀንነታችንን በኩራት እየገለፅን ነው ፡፡

መቼም ይሁን መች ድቀት ለአምባገነኖች የማያልፏት እጣቸው ነችና ዛሬ ከሰሜን አፍሪካዊቷ ቱኒዚያ የ26 ዓመት ወጣት የለኮሰው የነፃነት ሻማ ተቀጣጥሎ የባለሰለሣ ዓመታት ሥልጣን ስዶችን እያሳደደና እየቃጠለ እንደሚገኝ ሁሉም ተከታትሎታል ፡፡ ታድያ ከትናንትና ወዲያ ቱኒዚያ ትናንትና ግብፅን ዛሬ የሱዳን ወጣቶችን ያነሳሳ ሕዝባዊ አመፅ ነገ በኢትዮጵያችን እንደሚደገም የሚጠራጠሩ ካሉ ቤተመንግሥት የተወተፉ ዘመናዊ ወያኔዎችና ነፃነታችውን በፍርፋሬ የሸጡ ተለጣፊዎች ብቻ ናቸው ፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ !!

ይህንን ጥሪ ስናሰማ ለሐተታ ግዜ ስለሌለን ነው በአጭር ያደረግነው ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሕዝባዊ አመፅ ከተፋፋመባቸው የአፍሪካ አገሮች በባሰ መልኩ በገዛ ሀገሩ ባዳ የሆነ ዜጋ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ የለም ፡፡

እየጋፍነው ያለው የማያሽር የግፍ እንቆቆ ነውና እማኝ አንቆጥርም ፡፡ የትውልድም የሀገርም አደራ ያረፈብን የጀግናው የኢትዮጳያ ልጆች ነንና ታሪክ መሥሪያችን ጊዜ ከፊታችን ድቅን ብሏል ፡፡

በነፃነታችን ላይ ላለፉት 20 ዓመታት ያናጠረብንን ዘረኛ፥ አማቂ፥ ሙሰኛ፥ ክብር አዋራጅ፥ ህፃንንና መሬት ሻጭ ሥርዓት በሕዝባዊ አመፅ ለመናድ ዝግጁ እንሁን ፡፡ በተከታታይ ዘመናዊ ቴክኖሌጂ በፈጠራቸው መገናኛዎች በመከታተል ለምንጠራው ቁርጥ ያለ ዝምታ ሰባሪ አዋጅ በተጠንቀቅ ዘብ እንቁም ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት አባላት በያላችሁበት ክፍለ ሀገራት ይህ የተጠንቀቅ የሕዝባዊ አመፅ ጥሪ እንደደረሳችሁ ለዜጋ ሁሉ እንድታስተላልፉ አደራ እንላለን ፡፡ በተለይ በሳምንት ሁለት ቀን ረቡዕና እሁድ በሚተላለፈው የናት ድርጅታችን የኢሕአፓ ድምፅ በሆነው በፍኖተ ዲሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ እንድትከታተሉት በሕዝባዊ ፍቅር መልዕክታችንን እናስተላልፋለን ፡፡

ሕዝባዊ አመፃችን በቅርብ ይጠራል !!!

ታሪካዊው የየካቲት ስልሳ ስድስት ይደገማል !!!

የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሥርዓት ለውጥ ተዘጋጅተናል !!!

ኢወክንድ

ጥር 2003 ዓ.ም

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com

EPRPYL